# ያሰብከው ዓላማ
(ከማህሉ በቀለ ቶሮንቶ)

ያሰብከው ዓላማ፣ ግቡን ካልመታልህ
ችግሩ ከበዛ፣ ጠላት ካየለብህ
ጠላትህን ቀንስ፣ ወዳጅህን አብዛ
ታላቅ እቅድ አውጣ፣ ለእምነትህ ተገዛ
ጥበብን ፈልጋት፣ እውነትን ደግፋት
ዕብደትን ንቀፋት፣ ውሸትን ሰርዛት
ሰፋ አርገህ አስብ፣ ዕይታህ አይጥበብ
በዛፍ አትጣላ፣ ጫካ እንዳለ አስብ
አርቀህ ተመልከት፣ ራዕይ ይኑርህ
ሁልጊዜም ለዛሬ፣ ነገ አለ ብለህ
ትናንትን በማንሳት፣ አትሂድ ወደኋላ
ለአዲሱ ክረምት፣ እንዲሆን ከለላ
ቀይስ ጥሩ ዘዴ፣ ፍጠር አዲስ መላ
ወጤቱን እንድታይ፣ የኋላ የኋላ፡፡

ሥራና ሃሳብህ፣ ከጊዜው ጋር ይሁን
ፀፀትና ቁጭት፣ አሳሪህ እንዳይሆን
ትርጉም ያለው ሥራ፣ ትርጉም ያለው ህይወት
መሆኑን አትዘንጋ፣ የዕድገት መሠረት
ደግሞም ለብቻህን፣ አትሩጥ እንዳበደ
ወገን እንዳጣ ሰው፣ እንዳልተወደደ
ሥራህ ጥራት ካለው፣ ቃልህን ካከበርክ
ለህሊናህ እንጂ፣ ለሆድህ ካላደርክ
እንኳን ወዳጆችህ፣ አንተን የሚመስሉ
የሚፈሩህና፣ የሚጠሉህ ሁሉ
የሽነቆልሀል፣ አማራጭ ሲጠፋ
መኖር ሲሳናቸው፣ በጉራ በፉፋ
ከንቱ ሆኖ ሲቀር፣ እውነት ያሉት ተስፋ፡፡

ስሜትህ ይሚሚቅ፣ ጉልበትህ ይበርታ
አእምሮህ ያስተውል፣ ነገር በዝግታ
ለመፍረድ አትቸኩል፣ ሌላውን አትኮንን
በውሸት ጀብደኛ፣ ዝነኛ አትሁን
መቻቻልን ልመድ፣ ጥፋትህን ተቀበል
ለመቆ'ጠብ ሞክር፣ ከአጉል ቂም በቀል

ተመከር ተዘከር፤ ልቦናህን አፅዳ
ካለብህ ለወገን፤ ያልከፈልከው ዕዳ
አይኖችህን ፈጠጥ፤ ጆሮችህን ከፈት
እጆችህን ዘርጋ፤ አፍህንም ዝግት
አድርገህ ሞክረው፤ እስኪ ለእውነት ብለህ
የያዘህ አባዜ፤ ድንገት ቢሄድ ብለህ
ሐቁ ከውሸቱ፤ ተከፍሎ እንዲታይህ
የእውነት መክፈቻው፤ ቁልፉ እንዳይጠፋብህ፡፡

በዛም ሆነ በዚህ፤ የሰው ልጅ ነህና
ምንግዜም፤ ከኃጥያት አትፀዳምና
ትናንትና ዛሬ፤ ዘንድሮም አቻምና
ላይገርምህ ይችላል፤ የራስህ ስንፍና
የገዛ ጆሮህ፤ ጠላትህ ነውና፡፡

ለወገን ለአገር፤ ማሰብከን አታቁም
ለመብት ለነፃነት፤ መጮህክን አታቁም
ለሠላም ለፍትህ፤ መጮህክን አታቁም
ለዴሞክረሲያዊ ሥርዓት፤ መጮህክን አታቁም
ያብዛኛው ሕዝብ ምርጫ፤ ማሸነፉ አይቀርም
ትግልህና ድልህ፤ ብዙ አይራራቁም፡፡

ያች ውድ እናትህ፤ ኢትዮጵያ የሚሏት
በታሪክ በባህል፤ ጥንታዊነት ያላት
ከውስጥም ከውጭም፤ ብዙ ጠላት ያላት
የጀግኖች ያርበኞች፤ ያማኞች ወላጅ ናት፡፡

ይህን ተገንዝበህ፤ በታሪክህ ኮርተህ
ጊዜና ጉልበትህን፤ ባንድ ላይ አድርገህ
የጋራ ጠላትህን፤ በጋራ መክተህ
በተባበረ ኃይል፤ መብትህን አስከብረህ
የምትኖርበት ቀን፤ እጅጉን ተቃርቧል
የእናትህ መከራ፤ ማብቂያው ቀን ተዳርሷል
እውነትና ንጋት፤ እያደር ይጠራል
ዓላማህ ይሳካል፤ ድል ያንተ ይሆናል!

(የግጥሙ ፎርማት ማስኩሊን ቢሆንም ከወንድ ትምክህት ነፃ ነው፡፡ ሣ.በ.)